በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሰኔ ፲፫ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# <u>የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3</u>

## *የምስጢረ ንስሐ አፈጻጸም -ሥርዓተ ኑዛዜ*

### *ከኑዛዜ በፊት*

- የኑዛዜ ጊዜ ከአንድ ወይም ከአንድ ወር ተኩል በላይ መርዘም የለበትም። ኑዛዜን ማዘግየት ሰው ኃጢአቱን ሳይናዘዘው እንዲረሳውና ቸልተኛ እንዲሆን ያደርገዋል።
- ኑዛዜን ማዘግየት ለሰው ታላቅ ጥፋት ሲሆን መንፈሳዊ እድገቱንም ያቀጭጨዋል።
- አንዳንድ አባቶች ልጆቻቸውን ንስሐ የገቡበትን ጊዜ በማስታወሻ ደብተራቸው መዝግበው ይከታተላሉ። ይህም ልጆቻቸው በየጊዜው ንስሐ እንዲገቡ ያበረታታቸዋል።
- እያንዳንዱ ሰው ኃጢአቱን ከመናዘዙ በፊት ቁጭ ብሎ ራሱን በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልገዋል።
- ይህንም ኤርምያስ ‹‹የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኵላሊትንም እፈትናለሁ።›› *<u>ኤር 17፡9-10።</u>* እንደጻፈው በጸሎት ልንጀምረው እንችላለን።
- ለኑዛዜም ስንዘጋጅ ኃጢአታችንን እኛ ብቻ ልናነበው በምንችልበት መንገድ በትንሽ ወረቀት ላይ መጻፋችን የሚመከር ነው። ይህም ወረቀቱ በሌላ ሰው እጅ እንዳይወድቅ የሚረዳ ሲሆን ኃጢአታችንንም ሳንረሳ እንድንናዘዘውና እንድንተወው ያግዘናል።

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3

## *የምስጢረ ንስሐ አፈጻጸም -ሥርዓተ ኑዛዜ*

### *ከኑዛዜ በፊት*

- *ኃጢአቱን የሚናዘዝ ሰው ለሚከተሉት ሦስት ነገሮች ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡*

1. ስለ ሠራው ኃጢአትና ስህተት
2. ስለ መጥፎ ሐሳቡና ስሜቱ፡- ይህም ከመምህረ ንስሐችን ክፉና በጎን ለመለየት የሚያስችለን ምክር ለማግኘት ይረዳል፡፡
3. በመንፈሳዊ ሕይወቱ ዙሪያ ከንስሐ አባቱ ምክር ወይም መመሪያ የሚፈልግባቸውን ጥያቄዎቹን፡፡

- ራሳችንንም ስንመረምር (ስንገመግም) ታማኝነት፣ ኃጢአታችንን እያነሳን ምሕረትንም እየለመንን በራሳችን አንዲት ክፍል ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት ጸሎት ማድረግና፣ ኃጢአትን የምንናሸንፍበትን የእግዚአብሔርን ኃይል ማግኘት አስፈላጊ ናቸው፡፡
- *ሥርየት ልናገኝባቸው የሚገቡ ኃጢአቶችን በሦስት መንገድ መናዘዝ አለብን፡፡*

1. ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ልጄ ሆይ፥ ይህን አድርግ ራስህንም አድን፥ በጎረቤትህ እጅ ወድቀሃልና ፈጥነህ ሂድ፥ ጎረቤትህንም ነዝንዘው፡፡ለዓይንህ እንቅልፍን ለሽፋሽፍቶችህም እንጕልቻን አትስጥ፥እንደ ሚዳቋ ከአዳኝ እጅ፥ እንደ ወፍም ከአጥማጅ እጅ ትድን ዘንድ፡፡›› *ምሳ 6፡3-5፡፡* እንደተናገረው

# <u>የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3</u>

*የምስጢረ ንስሐ አፈጻጸም -ሥርዓተ ኑዛዜ*

*ከኑዛዜ በፊት*

- *ሥርየት ልናገኝባቸው የሚገቡ ኃጢአቶችን ሦስት ጊዜ መናዘዝ አለብን፡፡*

1. <u>በበደልነው ሰው ፊት መናዘዝ</u> የበደልነውን ሰው ይቅርታ ለማግኘትና በኃጢአቱም ውጤት ከሚመጣብን ጉዳት ለማምለጥ ይረዳናል፡፡ <u>*ማቴ 5፡23-24፡፡*</u>
2. ለሰው ሁሉ አባት በሆነውና በፊቱ በምንበድለው <u>በእግዚአብሔር ፊት መናዘዝ፡፡</u> ልበ አምላክ ዳዊት በኦርዮና በቤርሳቤህ ላይ ሲበድል እግዚአብሔርን እንደበደለ አድርጎ ቆጥሮበት ‹‹በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ?›› ሲለው ዳዊትም ‹‹እግዚአብሔርን በድያለሁ፡፡›› <u>*ካል ሳሙ 12፡፡*</u> በማለት መልሷል፡፡ በንስሐ መዝሙሩም ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹አንተን ብቻ በደልሁ፥ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ፥›› <u>*መዝ 50፡4፡፡*</u> በማለት በትሕትና ምሕረትን ለምኗል፡፡
3. <u>በካህኑ ውክልና በቤተ ክርስቲያን ፊት መናዘዝ፡፡</u> ቤተ ክርስቲያን እናት ስለሆነች ስለ ሰላምችን፣ ፍቅራችንና ከሌለች ጋር ማድረግ ስላለብን ስምምነት (እርቅ) ትጠነቀቅልናለች፡፡ ካህኑም የበደለውን ከተበደለው ጋር የሚያስታርቅ የሰላም ርግብ ነው፡፡ ካህኑ ኑዛዜያችንን የሚቀበል፣ ስለ በደላችንን ይቅርታ የተሾመ፣ የእግዚአብሔርን ምስጢራት የሚያስፈጽም

# <u>የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3</u>

## *የምስጢረ ንስሐ አፈጻጸም -ሥርዓተ ኑዛዜ*

## *ከኑዛዜ በፊት*

3. <u>በካህኑ ውክልና በቤተ ክርስቲያን ፊት መናዘዝ…</u> መልእክተኛ ነው፡፡ ካህኑ ለዚህም የሚሆን ቀኖና (ቅጣት) ይሰጠናል፡፡ ቀኖናችንንም ስንፈጽም ከበደላችን ይፈታናል፡፡ ከተፈታንም በኋላ ‹‹ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ፡፡›› <u>*ራእ 7፡14፡፡*</u> እንደተባለላቸው ቅዱሳን ‹‹የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናልና፡፡›› <u>*ቀዳ ዮሐ 1፡7፡፡*</u> የጌታችን የአማኑኤልን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን (ቁርባንን) መቀበል እንችላለን፡፡

## *በኑዛዜ ጊዜ*

- ኑዛዜ ፊትን ወደ ምሥዋዑ በመመለስ ኃይልና ቅዱስናን እንዳገኘን እንዲሰማን ሆነን በቤተ ክርስቲያን ቅጽር (ጥግ) መፈጸም አለበት፡፡
- ንስሐ የቤተ ክርስቲያን ምስጢር እንደመሆኑ መጠን በቤተ ክርስቲያን መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመምጣቱ ጥንካሬ የሌለው ቀድሞውኑ ርቆ የኖረ ኦርቶዶክሳዊ ሰው ንስሐ ሊገባ ቢወድ፣ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ የተያዘ ሰውም ቅዱስ ቁርባን ከመቀበሉ በፊት ንስሐ ሊገባ ቢወድ ወይም ያልታወቀ ምክንያት ያለው ቢኖር ካህኑ እቤቱ (ያለበት) ድረስ ሄዶ (ተገናኝቶ) ኑዛዜውን ሊቀበለው ይችላል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3

***የምስጢረ ንስሐ አፈጻጸም -ሥርዓተ ኑዛዜ***

***በኑዛዜ ጊዜ***

- ንስሐ አካላዊና መንፈሳዊ ዝግጅት የሚፈልግ የተቀደሰ ምስጢር ነውና ካህኑ ኑዛዜ ሲቀበል ማዕረገ ክህነቱን የሚገልጥ ልብስ መልበስ ይኖርበታል፡፡
- በቤተ ክርስቲያንም ንስሐ ሊገቡ የሚመጡ ተራቸውን የሚጠብቁበት ሊያነብቡዋቸው የሚችሉአቸው መጻሕፍት የሚገኙበት የመቆያ የመጠበቂያ ሥፍራ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- እንደሌሎቹ ምስጢራት ምስጢረ ንስሐም ሲፈጸም ካህኑ በጾም ቆይቶ (ሆኖ) ሊፈጽመው ይገባል፤ ይህም ማለት ኑዛዜ ሲቀበል ሳይበላና ሳይጠጣ ቆይቶ መሆን አለበት፡፡
- የሚናዘዘውም ምዕመን ወደ ካህኑ መጥቶ መስቀሉን ወይም እጁን ከሳመ በኋላ በአክብሮት በፊቱ መቀመጥ አለበት/አለባት፤ ካህኑ መንፈስ ቅዱስ ከርሱ ጋር ሆኖ የሚሠራ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና፡፡ *ዮሐ 20፡22-23፡፡*
- ከኑዛዜውም በፊት ካህኑና የሚናዘዘው ፊታቸውን በትእምርተ መስቀል ምልክት በማማተብ አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ገብርኤልን መጸለይ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመቀጠልም ካህኑ ስለ መንፈሳዊ ሕይወቱ በመጠየቅ እንዲናዘዝ መጋበዝ ይጠበቅበታል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3

## *የምስጢረ ንስሐ አፈጻጸም -ሥርዓተ ኑዛዜ*

### *በኑዛዜ ጊዜ*

- ንስሐ የሚገባውም ሰው ኑዛዜውን የጻፈበትን ወረቀት በመያዝ ያለምንም መሳቀቅና መጨነቅ አንድ በአንድ መናዘዝ፤ ካህኑ የሚሰጠውንም ምክርና ቀኖናም መቀበል ይኖርበታል። ከካህኑም ጋር የሚደረግ ውይይት በአክብሮትና በግልጽነት መከናወን አለበት።
- የሚናዘዘው ሰው የካህኑን የዋሕና ትሑት ልቦና ለመጠበቅ ከባዱን ኃጢአት በማስቀደም ቀለል ያሉትንም በማስከተል መናዘዝ ይገባዋል።
- ስንናዘዝም የካህኑን ጊዜ ብሎም ለኑዛዜ የሚጠባበቁ የሌሎችን ጊዜ ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል። ስለዚህ ወደ ሌላ ታሪክ ከመግባት መቆጠብ ይጠበቅብናል። በኑዛዜም የሚገኘውን መንፈስ ቅዱስና የምስጢሩን ታላቅነትና ማስተዋል ተገቢ ነው።
- ካህኑ የሚናዘዘውን ሰው ኑዛዜ ከማቃለልና ተስፋ ከማስቆረጥ መቆጠብ ይገባዋል። በሌላ በኩል ካህኑ ኑዛዜው እንዳይቃለል ቸልተኛ ከመሆንም መጠንቀቅ አለበት።
- ስለዚህ ካህኑ ጠቢብ፣ አስተዋይ የሚናዘዙትን ከኃጢአታቸውና ከውድቀታቸው በቀር የሚወዳቸው መሆን አለበት።

# <u>የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3</u>

*የምስጢረ ንስሐ አፈጻጸም -ሥርዓተ ኑዛዜ*

*በኑዛዜ ጊዜ*

- ከኑዛዜም በኋላ ተናዛዡ በካህኑ ሥር ተንበርክኮ ራሱን ዝቅ በማድረግ ‹‹እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ›› *<u>ሉቃ 18፡13፡፡</u>* የተባለውን ቃል እየደጋገመ መመለስ አለበት፡፡
- ካህኑም በቀኝ እጁ መስቀሉን ተተናዛዡ ራስ ላይ በማድረግ የንስሐ ጸሎትን ይጸልያል፡፡

<u>ማስታወሻዎች</u>

- ካህኑ በተናዛዡ ራስ ላይ ጌታችን ደሙን ስለርሱ ያፈሰሰበትን መስቀል አኑሮ ይጸልይለታል፡፡ ተናዛዡም በራሱ ላይ ካረፈው መስቀል ክብር፣ በካህኑ አድሮ ሥጋውና ነፍሱን ከኃጢአቱ ሊያነጻ ከቀረበው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብሎም ከተጫነው ከኃጢአት ብዛት የተነሳ ያጎነብሳል፡፡
- በዚህም መንገድ በመቀጠል ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ፡፡›› *<u>ካል ቆሮ 5፡18-19፡፡</u>* በማለት እንደተናገረው በተናዛዡና በእግዚአብሔር መካከል በካህኑ አማካኝት እርቅ ይደረጋል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 3

## ማስታወሻዎች

- ካህኑ የተነሳሒውን ያጎነበሰ ራስ በመስቀሉ ተጭኖ ግንባሩን በእጁ ይዞ መጸለዩ ሁሉን በእጆቹ እፍኝ የያዘ የእግዚአብሔርን አሐዜ ኩሉ መሆንና ተነሳሒውም ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ይቅር የተሰኘችለት እንደምትሆን የሚያመለክት ነው።
- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን›› *ካል ቆሮ 10፡5* እንዳለ እግዚአብሔር ሁሉን የሚቆጣጠርና ወደ ወደደውም መልካም ጎዳና ሁሉ የሚመራ ነው።
- ካህናቱ ‹‹እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።›› *ቀዳ ቆሮ 2፡16።* ያለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል በተግባር የሚተረጉሙ ‹‹ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል።›› *ራእ 22፡4።* አገልጋዮች ናቸውና የክርስቶስን ፈቃድ በምዕመናኑ ልቦና ያስፈጽማሉ።
- በመጨረሻው ተናዛዡ መዝሙር 50ን ይጸልይ። ‹‹አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፥ ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና። አንተን ብቻ በደልሁ፥ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ፥ በነገርህም ትጸድቅ ዘንድ በፍርድህም ንጹሕ ትሆን ዘንድ። እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ። እነሆ፥ እውነትን ወደድህ የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ። በሂሶጵ እርጨኝ፥ እነጻማለሁ እጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ። ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፥ የሰበርሃቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል። ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፥ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ። አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ። ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ። የማዳንህን ደስታ ስጠኝ፥ በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ። ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተምራለሁ፥ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ። የመድኃኒቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ከደም አድነኝ፥ አንደበቴም በአንተ ጽድቅ ትደሰታለች። አቤቱ፥ ከንፈሮቼን ክፈት፥ አፌም ምስጋናህን ያወራል። 5116መሥዋዕትን ብትወድድስ በሰጠሁህ ነበር የሚቃጠለውም መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም። የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥ የተሰበርውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም። አቤቱ፥ በውዴታህ ጽዮንን አሰማምራት የኢየሩሳሌምንም ቅጽሮች ሥራ። የጽድቁን መሥዋዕት መባውንም የሚቃጠለውንም መሥዋዕት በወደድህ ጊዜ፥ ያን ጊዜ በመሠዊያህ ላይ ፍሪዳዎችን ይሠዋሉ።››

# ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org